# «ውሸታም!»

መክብብ ማሞ(mekbma@yahoo.com)

ሰሞኑን የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት የሳበ አንድ ክስተት በአሜሪካ ተፈጽሟል:: ፕሬዚዳንት ኦባማ በምርጫ ዘመቻቸው ጊዜ ቃል የገቡለትን የጤናጥበቃ ማሻሻያ አዋጅ እንዲጸድቅ የሕዝብ ተወካዮችን ሰብስበው ምክርቤት ንግግር በሚያደርጉበት ወቅት ከተቃዋሚ የሪፓብሊካኑ ወገን የማርጎምገምና የተቃውሞ ድምጽ ይሰማ ነበር:: በተለይ ግን አዲሱ የጤና ማሻሻያ አዋጅ «ሕገወጥ ስደተኞችን አያካትትም» የሚል ንግግር ባደረጉ ጊዜ ከደቡብ ካሮላይናው ተወካይ «ውሸታም!» የሚል ድምፅ ተሰማ::

እንደእውነቱ ከሆነ በረቂቅ ህጉ ላይ ሕገወጥ ስደተኞች የጤና መድህን ዋስትና እነማያገኙ በማያሻማ መልኩ የሰፈረ ጉዳይ ነው:: እዚህ ላይ ማነው ውሸታም የሚለውን ለመመርመር አይደለም ጽሁፌን በዚህ መግቢያ የጀመርኩት:: ሆኖም ግን ይህንን የሰማሁ ምሽት እንደራሴው ኢትዮጵያ ቢሆኑ ኖሮ ከምርጫ 97 ጀምሮ እስካሁን ድረስ ምን ያህል ጊዜ «ውሸታም!» እያሉ ይጮኹ ይሆን በማለት ያለፉትን አምስት ዓመታት በምናቤ መቃኘት ጀመርኩና ከዚህ በፊት የተደረጉ ቃለመጠይቆችን ለመመርመር ወደኋላ ሄድኩ::

ማርክሲስታዊው ህወሃት ከጫካ ወጥቶ የምኒልክን ቤተመንግሥት ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 18 ዓመታት ከአመራሮቹ ስንሰማ የቆየነው ውሸት ጆሮ የሚገነጥል ሲሆን በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጽ ከተሰረቀበት 1997 ዓም ጀምሮ «ጠቅላይ ሚኒስትሩ» ለተለያዩ ምዕራባዊ የመገናኛ ብዙሃን «ሥልጣኔን እለቃለሁ» በማለት ሲሰጥ የነበረው ከቁጥር በላይ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ጥቂቱን ግን ከዚህ በታች አቅርቤዋለሁ::

የቢቢሲው ጋዜጠኛ ስቲፈን ሳኩር ከምርጫ 97 በኋላ ለ«ጠቅላይ ሚኒስትር» ዜናዊ ሰኔ 27 ቀን 1997 ቃለመጠይቅ ባደረገበት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቆት ነበር::

**ስቲፈን:-** አሁን ስላለው አጀንዳ እንድጠይቅ ይፈቀድልኝ:: እንደው እንበልና የምርጫው ውጤት ፓርቲህን አሸናፊ አደረገው እንበል እና ይህ ከሆነ እንደገና ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት እንደገና በሥልጣን ላይ ትቆያለህ?
**ዜናዊ:-** ያ ፓርቲዬ የሚወስነው ጉዳይ ነው::

**ስቲፈን:-** አንተ ግን ምን ለማድረግ ነው የምትፈልገው?
**ዜናዊ:-** እኔ ማድረግ የምፈልገውን ቆየት ብዬ የማስብበት ነው:: ውሳኔዬም በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው::

**ስቲፈን:-** በእርግጥ ማድረግ የምትፈልገውን ወስነሃል:: ማለቴ ለመመረጥ ተወዳድረሃል ይህም ማለት ሥልጣኑን ትፈልገዋለህ?
**ዜናዊ:-** ሥልጣኑን የምፈልገው አገሬን ለማገልገል ነው:: የማገለግለው ግን የምጨምረው እሴት ሲኖር ነው . . . የምጨምረው እሴት አለኝ ፤ ይህንንም እቀጥልበታለሁ የምጨምረው እሴት እስካለኝ ድረስ:: በተመሳሳይ መልኩ ፓርቲዬ እሴት የማልጨምር መስሎ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊቀይር ይችላል::

# «ውሸታም!»

ምርጫውን ህወሃት ካጭበረበረ 1 ዓመት ከ7 ወር በኋላ የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጠኛ ስቴፋኒ ማክሩመን ታህሳስ 5 ፣ 1999 ዓም ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርባ ነበር::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

**ስቴፋኒ:-** ለሦስተኛ ጊዜ ለመመረጥ ዕቅድ አለህ?
**ዜናዊ:-** ፓርቲዬ? ፓርቲዬ ለሦስተኛ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለአስረኛ ጊዜም ሊሞክር ይችላል::

**ስቴፋኒ:-** አንተስ በግልህ?
**ዜናዊ:-** እኔ በግሌ ይበቃኛል ነው የምለው::

## «ውሸታም!»

ቀጥሎም ከዘጠኝ ወር በኋላ አሌክስ ፔሪ ከ«ታይም» መጽሔት ጳጉሜ 1፤ 1999 የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበ::

**አሌክስ:-** አብዛኛውን ጊዜ የአፍሪካ መሪዎች ሥልጣን ለመልቀቅ ሲያመነቱ ይስተዋላሉ:: ሆኖም ግን ከዚህ በፊት በሥልጣን እንደማትቀይ ፍንጭ ስትሰጥ ቆይተሃል?
**ዜናዊ:-** አሁን ሦስት ዓመት ብቻ ነው የቀረኝ::

**አሌክስ:-** ከዚያ ከሥልጣንህ ትለቃለህ?
**ዜናዊ:-** ከዚያማ ሂደቱ ይቀጥላል::

**አሌክስ:-** ለምንድነው ሥልጣን መልቀቅ የምትፈልገው?
**ዜናዊ:-** እስካሁንም ብዙ ቆይቻለሁ:: ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ አዲስ ነገር ለማድረግ የማስብበት ይሆናል::

## «ውሸታም!»

ቀጣዩን ቃለመጠይቅ ሲያደርግ ደግሞ ሦስት ወር እንኳን አልሞላም ነበር:: ጠያቂው የአልጃዚራው መሃመድ አዶው ኅዳር 12 ፤ 2000 ዓም ያደረገው ነበር::

***መሃመድ:-*** በቅርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥልጣን የመልቀቁን ጉዳይ እያሰብክበት ነውን?
**ዜናዊ:-** ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት በጠቅላይ ሚኒስትርነት የማገለግልበት ይህ የመጨረሻው የሥልጣን ዘመኔ ነው::

## «ውሸታም!»

በዚሁ በ2000 ዓም ግንቦት 4 ቀን **awate.com** ከተሰኘ ድረገጽ ጋር ቃለምልልስ ያደረገ ሲሆን ጠያቂውም ሳሌህ ጆሃር ነበር::

**ሳሌህ:-** በህይወት ዘመኔ ከሥልጣንህ ለቅቀህ «የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር» እየተባልክ በመጠራት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማስተማር ፤ መጽሃፍ በመጻፍ ወይም አንድ ፋውንዴሽን ስትመራ የማይበት ጊዜ ይመጣ እንደሆን እስቲ ንገረኝ::
**ዜናዊ:-** በጣም ትክክል ነው:: እኔም ያንን ቀን እየናፈኩት ነው:: ሩቅ እንደማይሆን አስባለሁ::

**ሳሌህ:-** ይህ ማለት እንግዲህ ለሌሎች ሁሉ ምሳሌ ትሆናለህ ማለት ነው?

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

**ዜናዊ፡-** ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ነገን ልትኖረው እንደምትችል እርግጠኛ ልትሆን አትችልም፡፡ ሆኖም ግን እንደማንኛውም ሰው እኖራለሁ ብዬ በማሰብ ከሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በኋላ «የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር» ብለህ ልትጠራኝ ትችላለህ፡፡

## «ውሸታም!»

ውሸቱ ግን በዚህ አላቆመም፡፡ ባለፈው ዓመት መጋቢት 24 ፥ 2001 ዓም የቢቢሲዋ ዘይነብ ባዳዊ ቃለመጠይቅ ባደረገችለት ጊዜ ይህንኑ ከሥልጣን የመልቀቅ ጥያቄ አንስታ ነበር፡፡

**ዘይነብ፡-** ከዚህ በፊት እንደጠቆምኩት ከ1983 ዓም ጀምሮ በሥልጣን ላይ ነበርክ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከሥልጣንህ የምትለቅበት ጊዜ እንደደረሰ ስትናገር ቆይተሃል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ራስህን የፓርቲህ ወታደር አድርገህ ስትናገር ትደመጣለህ፡፡ መቼ ነው እርግጠኛ ውን ቀን የምትነግረን? ምክንያቱም ከምናየቸው ነገሮች ይሄ በአፍሪካ መሪዎች ዘንድ የሚታየውን «ያለኔ . . . » የሚለውን የአፍሪካ መሪዎችን አስተሳሰብ ተደግፋለህ እንድል እያደረከን ነው ያለኸው፡፡ ማለትም ምትክ የሌለው መሪ ዓይነት ፥ ለሁለት ዓስርተ ዓመታት በሥልጣን ቆይቻለሁ የሚል ዓይነት?
**ዜናዊ፡-** ራሴን ምትክ የሌለው መሪ አድርጌ አላውቅም፡፡ እናም ማንኛውም ሰው ራሱን ለፓርቲም ሆነ ለአገር ምትክ የሌለው አድርጎ የሚቆጥር ከሆነ ያ ፓርቲም ሆነ አገር መኖር ይገባዋል ብዬ አላምንም፡፡

**ዘይነብ፡-** ታዲያ መቼ ነው ቁርጥ ያለውን ቀን የምትናገረው?
**ዜናዊ፡-** ፓርቲዬ ካቀረብኩት ዕቅድ ጋር ሲስማማ ያኔ ይሆናል፡፡

**ዘይነብ፡-** ዕቅድህ ምን እንደሆነ ልትነግረን ትችላለህ? በ2002 ዓም ምርጫ ይካሄዳል?
**ዜናዊ፡-** ዕቅዴማ ይህ የመጨረሻው የሥልጣን ዘመኔ እንደሚሆን ማረጋገጥ ነው፡፡

## «ውሸታም!»

ከጥቂት ወራት በፊት ሰኔ 10፥ 2001 ዓም የፋይናንሺያል ታይምስ የአፍሪካ ቢሮ አርታኢ የሆነው ዊሊያም ዋሊስ ይህንኑ ማለቂያ የሌለውን የሥልጣን መልቀቅ ጥያቄ አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም አጠያየቁን ቀየር አድርጎት ስለነበር የውሸቱ ለከት የት እንደደረሰ በግልጽ እንዲያሳይ አድርጎታል፡፡

**ዊሊያም፡-** ከዚህ ቀደም ከሥልጣን ለመውረድ ፈቃደኛ እንደሆንክ ስትናገር ቆይተሃል፡፡ በዚህ ዙሪያ ያለውን እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ብታስረዳን?
**ዜናዊ፡-** በአሁኑ ጊዜ በፓርቲያችን ውስጥ ውይይት እያደረግን ነው፡፡ ይህም በፓርቲያችን ውስጥ የምናደርገው ውይይት ሰዎች ሊገምቱ ከሚችሉት በላይ በጣም ብስለት የተሞላበት ነው፡፡ ስለመለስ ብቻ አይደለም የምንነጋገረው፡፡ በትጥቅ ትግሉ የተሳተፈው የቀድሞው ትውልድ በአዲስና የትጥቅ ትግል ተሞክሮ በሌለው ትውልድ እንዴት ሊተካ ስለሚችልበት ሁኔታ እየተወያየን ነው፡፡ ለፓርቲያችን ሲባል ይህ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ታክቲክን በተመለከተ ማለትም ጊዜው መቼ ይሆናል የሚለው ቁርጥ ያለ መልስ ላይኖር ይችላል፡፡ ክርክሩም በዚሁ የሚቀጥል ነው፡፡ ሆኖም ግን የቀድሞው አመራር በአዲስ አመራር መተካት አለበት በሚለው ላይ ግን አለመስማማት የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ ይህ ከመፍትሔዎቹ አንዱ ነው ፥ ብቸኛው መፍትሔ ግን አይደለም፡፡ ስለዚህም የእኛ ንቅናቄ በአመዛኙ ሌሎች ንቅናቄዎችን ከሚያጋጥማቸው የመፈረካከስ አደጋ አምልጧል ብዬ አምናለሁ፡፡

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

**ዊሊያም:-** እናም የሚቀጥለው ዓመት በሚደረገው ምርጫ አትወዳደርም ማለት ነው?
**ዜናዊ:-** እያልኩ ያለሁት እኔ በግሌ ይበቃኛል ነው የምለው:: እኔ ብቸኛው ተኳሽ አይደለሁም:: ለበርካታ ጊዜያት ጠቅላይ ሚኒስትር በነበርኩበት ጊዜም በድምጽ ብልጫ በመሸነፍ የማልፈልገውን ነገር ሳደርግ ቆይቻለሁ:: በተለይም በኤርትራ ጦርነት ወቅት ሳልፈልገው የማልስማማበትን ሆኖም ግን የፓርቲዬን ውሳኔ በመሆኑ ብቻ ያንን ሳስፈጽም ኖሬያለሁ:: በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ወቅት ሁለት አማራጮች አሉኝ:: ከሥልጣን መልቀቅ ወይም የብዙሃኑን ውሳኔ መቀበል:: ይህ ሲሆን እኔ የራሴን አቋም አቀርባለሁ ሌሎችም የራሳቸውን አቋም ያቀርባሉ ፤ ክርክሩም ይቀጥላል:: ተስፋ የማደርገው ሁላችንም አንድ የመግባቢያ ነጥብ ላይ እንደርሳለን ብዬ ነው:: ያም ሲሆን እኔም ህይወቴን ሙሉ ከተዋጋሁለት ፓርቲዬ መልቀቅ ሳያስፈልገኝ እንድቀጥል ይሆናል:: ከመንግሥት ሥልጣኔ ከለቀኩ በኋላም እንኳን በፓርቲዬ አባልነት መቀጠል እፈልጋለሁ:: እናም ተስፋ የማደርገው ሁላችንም አንድ የመግባቢያ ነጥብ ላይ እንደርሳለን ብዬ ነው:: ልዩነቶቻችን ደግሞ ያንን ያህል ትልቅ አይደሉም::

**ዊሊያም:-** ታዲያ ያ የሚሆነው መቼ ነው? በቅርቡ የምታደርጉት የፓርቲ ስብሰባ አላችሁ እንዴ?
**ዜናዊ:-** አዎን መስከረም ላይ ስብሰባ አለን::

**ዊሊያም:-** እናም ያኔ ነው በውሳኔው ላይ የምትከራከሩት?
**ዜናዊ:-** አዎን ግን ከዚያ በፊት ውይይቱ ይካሄዳል:: . . .

**ዊሊያም:-** ወደፊት ማነው የሚተካህ?
**ዜናዊ:-** ያንን ውሳኔ ለፓርቲው እተወዋለሁ:: . . .

**ዊሊያም:-** ኢትዮጵያውያን ለምንድነው በእርግጥ ሥልጣንህ እንደምትለቅ የማያምኑት?
**ዜናዊ:-** ምክንያቱም ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ሲደረግ ስላላዩ ነው::

**ዊሊያም:-** ነገር ግን እያደረክ ያለው ያንኑ የሚከተል እንደሆነ ነው::
**ዜናዊ:-** እኔ ይህንን ዓይነት አስተሳሰብ ለማስወገድ ነው የምፈልገው:: . . .

**ዊሊያም:-** እናም ይህ ማለት ሙሉ በሙሉ ከማንኛውም ተግባር ትገለላለህ ማለት ነው?
**ዜናዊ:-** ያ ካልሆነማ የአመራር ለውጥ ሊኖር አይችልም:: ነገር ግን ያንን ካደረግን በኋላ ፓርቲዬ ወይ መጽሃፍ እያነበብኩና እየጻፍኩ እንድቀመጥ ወይም ሌላ የፓርቲ ሥራ እየሠራሁ እንድቀጥል ይወስናል::

**ዊሊያም:-** የፓርቲ ሥራ ማለት ሊቀመንበርነት?
**ዜናዊ:-** አይመስለኝም ምክንያቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፓርቲው ሊቀመንበር መሆን አለበት:: ያ ደግሞ ጡረታ ለወጣ ሰው ሊሰጠው የሚገባ ሥልጣን አይደለም::

# «ውሸታም!»

እንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዚህ ዓይነት ቅጥፈት ላለፉት 18 ዓመታት በተለይም ደግሞ ላለፉት አምስት ዓመታት ሲነገረው ቆይቶ ያለፈው ሳምንት ህወሃት የሚቆጣጠረው ቴሌቪዥን ለአዲስ ዓመት አዲስ ዜና - ትኩስ ዜና - ሰበር ዜና ሰበረለት:: «ምትክ አልባው ጠቅላይ ሚኒስትር ከመጪው 2002 ምርጫ በኋላ ለቀጣዮቹ 5 ዓመታት ሥልጣናቸውን እንዳራዘሙትና . . . » የሚገርመው ሥልጣኑ መራዘሙ አይደለም ነገርግን አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንሳተፍበታለን የሚሉት ምርጫ ካሁኑ የተጠናቀቀ መሆኑን አለመገንዘባቸው ነው::

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com